# የፍትህ ሚኒስቴር

# የመብቶች መግለጫ

## ዕድሜያቸው ከ 10 እስከ 13 አመት ያሉ ታዳጊዎች ሲታሰሩ የሚሰጥ

**ይህ መረጃ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ሊሰጡት ይገባል።**
**ከእርስዎ ፍላጎት ጋር የማይቃረን ከሆነና የህግ ሂደቱ ላይ ተፅዕኖ የማያሳድር ከሆነ የወላጅነት ኃላፊነት የያዙ ሰዎች ተመሳሳይ መረጃ ይሰጣቸዋል።**
**በህግ ጥላ ስር በሚቆዩበት ግዜ ሁሉ ይህ ዶክመንት ከእርስዎ ጋር ሊቆይ ይችላል።**

በህግ ጥላ ስር የሚገኙት ከባድ እና ተደጋጋሚ ከ 5 አመት በማያንስ እስር ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል ፈፅመዋል ወይም ለመፈፀም ሞክረዋል የሚል ማሳያዎች በመኖራቸው ምክንያት መሆኑ ተነግሮዎታል።

ፈፅመዋል ተብለው ስለተጠረጠሩበት ወንጀል አይነት፣ ስለተፈጸመበት ቦታ እና ግዜ፣ እንዲሁም በህግ ጥላ ስር ምክንያት የማወቅ መብት አሎት።

ስለነዚህ ነገሮች እስከ 12 ሰዓታት ሊቆይ በሚችለው በቁጥጥር ባሉበት ግዜ ውስጥ ይነገርዎታል።

ይህ ግዜ ሲያልቅ አቃቤ ህግ (ወይም ጉዳዩን የሚያየው ዳኛ ወይም የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) በቁጥጥር ስር የሚውሉበትን ግዜ ለተጨማሪ አስራ ሁለት ሰዓታት ሊያራዝሙው ይችላል። ከዚያም ሁኔታዎች ካልከለከሉ በስተቀር እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቪዲዮ ኮንፍረንስ እዚህ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ።

በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ሲጠናቀቅ በአቃቤ ህግ (ወይም ጉዳዩን በሚመለከተው ዳኛ ወይም በታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) ውሳኔ መሰረት ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ወይም ሊለቀቁ ይችላሉ።

## በተጨማሪም፤ የሚከተሉት መብቶች እንዳሎት ተነግሮዎታል፡-

### ለተወሰኑ ሰዎች ስለሁኔታው ማሳወቅ

ወላጆችዎ ወይምወይም ሞግዚትዎ ወይም በአድራነት የሚመለከትዎት ግለሰብ ወይም ድርጅት በህግ ጥላ ስር የዋሉበትን ሁኔታ፣ ምክንያት፣ ግዜ እና ቦታ እንዲሁም ስለተጠረጠሩበት ወንጀል ሁኔታ እንዲያውቁ ይደረጋል።

አብሮት ለሚኖር ሰው ወይም፣ ከወላጅዎ ለአንዳቸው፣ ወይም ከወንድሞችዎ አልያም እህቶችዎ ወይም ከሞግዚትዎ ለአንዳቸው በህግ ጥላ ስር ስላሉበት ሁኔታ በስልክ ማሳወቅ ይችላሉ።

የውጭ ዜጋ ከሆኑ፤ ለሀገርዎ ቆንጽላ ኃላፊዎች ማሳወቅ ይችላሉ።

ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ካልኖሩ በስተቀር እነዚህ ጥያቄዎችዎ ባነስዋቸው ከ 3 ሰዓት በማይበልጥ ግዜ ውስጥ ይስተናገዳሉ።

### ከግለሰብ ጋር ስለመገናኘት

በህግ ቁጥጥር ስር እርስዎ እንደዋሉ ከተነገራቸው ሰዎች ከአንዳቸው ጋር በጽሁፍ፣ ስልክ ወይም ፊት ለፊት ለመገናኘት መጠየቅ ይችላሉ።

ጥያቄዎ በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ምክንያት ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ፤ ወይም ወንጀል እንዲፈጸም መንገድ የሚከፍት ከሆነ መርማሪ ኦፊሰሩ ጥያቄዎን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል። የተጠቀሰው ኦፊሰር ወይም እሱ የሚሾመው ግለሰብ የሚያደርጉት ግንኙነት በእርሱ ቁጥጥር ስር፤ እንዲሁም በምን አይነት ሁኔታ እና ለምን ያህል ግዜ ከ 30 ደቂቃ በማይበልጥ መደረግ እንዳለበት ይወስናል።

### በዶክተር ስለመመርመር

አቃቤ ህጉ (ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ወይም የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) የሚመረምርዎትን ዶክተር ይመድብልዎሎታል። የእስር ግዜው ከተራዘመ፤ አቃቤ ህጉ (ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ወይም የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) የሚመረምርዎትን ዶክተር በድጋሚ ይመድብልዎሎታል።

### ቃል መስጠት፣ ጥያቄ መመለስ ወይም ዝም ማለት

ማንነትዎን ካረጋገጡ በኋላ፤ ክስዎ በሚካሄድበት ግዜ የሚከተሉት መብቶች አሎት፡-

- ቃል መስጠት
- ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ መስጠት
- ወይም ዝም ማለት

## ከህጋዊ ወኪልዎ ጋር ስለመቅረብ

ስልጣን ያለው አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በክስ ሂደትዎም ሆነ በቃለ ምልልስ ወቅት የወላጅነት ስልጣን ካለው አካል ጋር አብረው ይቀርባሉ። አስፈላጊ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ከሚሾመው አዋቂ ሰው ጋር ወይም እርስዎ ከሚመርጡት ሌላ አዋቂ ጋር አብረው ሊቀርቡ ይችላሉ።

## የጠበቃ ድጋፍ ስለማግኘት

**የግድ በጠበቃ መደገፍ አለብዎት**

### የጠበቃ ምርጫ

በቁጥጥር ስር ከዋሉበት ግዜ አንስቶ፣ በክስ ሂደትዎ ግዜ፣ እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ እና በተራዘመበት በማንኛውም ግዜ ከመረጡት ጠበቃ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። ጠበቃ መቅጠር ካልቻሉ ወይም የመረጡት ጠበቃ ሊገኝ የማይችል ከሆነ አቃቤ ህጉ (ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ወይም የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) ወዲያውኑ ጠበቃ ተመድቦ እንዲያግዝዎ መጠየቅ ይችላሉ።

ጠበቃዎ በወላጆችዎወይም፣ በሞግዚትዎ ወይምወይም አደራ በተሰጠው ድርጅት ሊሾምልዎ ይችላል።

### የህግ ድጋፍ እና የምላሽ ግዜ

የውይይቱን ምስጢራዊነት በጠበቀ መልኩ ጠበቃዎ ለ 30 ደቂቃ ሊያገኝዎ ይችላል። በቁጥጥር ስር የሚውሉበት ግዜ ከተራዘመ፤ ጠበቃዎን በድጋሜ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ።

በእርስዎ ጥያቄ መሰረት ጠበቃዎ እርስዎ የሚሳተፉባቸውን የክስ ሂደቶች፣ክርክሮች፣ምልልሶች ወይም ማንነትን የመለያ ውይይቶች ላይ መሳተፍ ይችላል።

ይህ በሚሆንበት ግዜ፣ ማንነትዎን ለመለየት ከሚደረጉ ጥያቄ እና መልሶች ውጪ የመጀመሪያ ችሎትዎ ጠበቃዎ ስለ ችሎቱ ከተነገራቸው 2 ሰዓት እስከሚያልፍ ድረስ ጠበቃዎ ባሌሉበት ችሎት አይካሄድም። ነገር ግን የምርመራው ሁኔታ የሚያስገድድ ከሆነ በአቃቤ ህግ ወይም (ጉዳዩን በሚያየው ዳኛ ወይም በታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ) ፍቃድ የክስ ሂደትዎ ጠበቃዎ ባሌለበት ወዲያውኑ ሊጀምር ይችላል።

ክስ ማንበብ ወይም ክርክር እየተካሄደ ባለበት ግዜ ጠበቃዎ ከደረሰ፤ ከጠበቃዎ ጋር ይነጋገሩ ዘንድ ሂደቱ ይቆማል።

## የትርጉም አገልግሎት ስለማግኘት

ፈረንሳይኛ የማይናገሩ ወይም የማይገባዎት ከሆነ ከክፍያ ነጻ በሆነ መልኩ በክስዎ ሂደትም ሆነ ከጠበቃዎ ጋር በሚነጋገሩበት ግዜ የትርጉም አገልግሎት የማግኘት መብት አሎት።

## እስር እንዲቋረጥልዎት ስለማመልከት

ዳኛው እስር በማራዘም ጉዳይ ላይ ውሳኔ በሚሰጥበት ግዜ፤ አቃቤ ህጉን ወይም ጉዳዩን በሚያየው ዳኛ ወይም በታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዳኛ እስሩ እንዳይራዘም መጠየቅ ይችላሉ።

## ከጉዳይዎ ጋር የሚገናኙ የተወሰኑ ነገሮችን የማግኘት መብት

በእርስዎ ወይም በጠበቃዎ ጥያቄ መሰረት እና በህግ ጥላ ስር የሚቆዩበት ግዜ ከመራዘሙ በፊት የሚከተሉትን መጠየቅ ይችላሉ፡-

- በቁጥጥር ስር መዋልዎን የሚገልፅ መግለጫ
- የመረመርዎ ዶክተር የሰጠው የህክምና ሰርቲፊኬት
- የክስ ሂደትዎ-ጉባኤ

## አቃቤ ህጉን ስለማናገር

በቁጥጥር ከዋሉበት ግዜ አንድ አመት በኋላ መቀበልዎን በሚያረጋግጥ ድብዳቤ ወይም መቀበልዎን ለመዝገብ ቤት በማሳወቅ የክስዎን ፋይል ለማየት አቃቤ ህጉን መጠየቅ ይችላሉ።

## የሚስጥራዊነት መብት

የቴክኒክ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የክስ ሂደትዎ በፊልም ይቀረጻል። እነዚህን ቅጂዎች እንዲያስተላልፍ ለማንም አይፈቀድም።

ቅጂዎቹ የሚታዩት በችሎት ግዜ ሲሆን የክስ ሂደቱን ቃለ ጉባኤም ሆነ እርስዎን ሊያስለይ የሚችል ምንም አይነት ነገር እንዲታተም አይፈቀድም።